ማኅሌተ ጽጌ

ሰቆቃወ ድንግል
ነግሥ ዘሥርወተ ማኅሌት
መልክአ ውዳሴ ዘሰባቱ ዕለታት
ግእዝና ዐማርኛ



ተርጓሚ፡- ቀሲስ ልዑል ታመነ (መጋቤ ሐዲስ)
አርታዒ፡- ዲ/ን ግርማ ገሃዩ

አሳታሚና አከፋፋይ፡-
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፲፫ ዓ.ም.



ክረምቱ አለፈ!
በጋው ተተካ!
ምድር በአበቦች ውበት ተጌጠች /ተሸለመች፤
ሙሽሪት ሙሽራዋን ወንድሜ፤
ወልድ (ሙሽራው/ ወደ ተክል ቦታ ወረደ አለች::

ክፍል አንድ

1. አበባ ታየ

ከገብርኤል ሰላምታ ቃል ጋር ባመሰገነሽ ሰው፤
አጽም አበባ /ጽጌ/ በቅሎ ታየ፤
የጌታዬ እናቱ ማርያም ሆይ የምስጋና ጣዕመ መዓዛ በመሰጠኝ ጊዜ፤
ማኅሌተ ጽጌ በሚባል ምስጋናሽ፤
ለተአምርሽ ምስጋና አቀርባለሁ::

2. ማርያም ሆይ ሰላምሽ

ማርያም ሆይ ሰላምታሽ የምልክት ዕፅ አበቀለች፤
ከሞተ ሰው አፍም /አበባን /ጽጌ/ አወጣች አሳበበች፤
ከሁሉም ምስጋና እሷ ትበልጥብኛለችና፤
ይህችን የማኅሌተ ጽጌ ምስጋና አታስቸኩዩ ብለሽ፤
ለምትወጃት አንዲት ሴት ፍቅርሽን አስተማርሻት::

3. አንድ ሰው

ወደገዳም የሔደ አንድ ሰው፤
ዘወትር እንዳስለመደ የሰላምታሽን ቃል በሚያነብ ጊዜ፤
የሰማይ ንግሥት ማርያም ሆይ! ወደምድር ወረደሽ፤
የምስጋና አበባን ከአፉ ስትቀበዪ፤
ተአምርሽን ያየ ሁሉ አደነቀ።

4. ማርያም ሆይ መውደድሽን አውቄ

ማርያም ሆይ የጽጌረዳ አበባን የሚያስገኝ፤
የመልአክ ሰላምታ ለአንቺ ዘወትር እንደሚገባ መውደድሽን
አውቄ፤
ከገብርኤል ጋራ እንደ ገብርኤል ካመሰገንኩሽ ከእኔ፤
ከአንደበቴ የምስጋና ሽቶ አበባን ትሰበስቢ ዘንድ፤
የበጐነትሽን ምልክት ከእኔ ጋር አድርጊ።

5. መቆም አላፍርም

በማያልቅ ምስጋናሽ አብዝቼ ላመሰግንሽ፤
ዘመነ ጽጌ ቢያልቅም በሥዕልሽ ፊት መቆምን አላፍርም፤
ማርያም ሆይ ተአምርሽ እንደሚያስረዳው፤
ስም አጠራርሽ የወደቀውን ያስነሣል፤
ኃጢአተኛውንም ያጸድቃል።

6. ማርያም የፍቅርሽ ቀን

ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ቀን በልቡናየ ተሾመ ተመረመረ፤
የአበባ ደም ግባትሽ ጥላም በሕሊናየ ተዋሐደ፤
አዲስ ምስጋናሽን ተአምርሽንም እናገር ዘንድ፤
መንፈስ ቅዱስን ከተሞሉ ከንፈሮችሽ፤
በከንፈሮቼ ሞገስን አፍስሽ።

7. እንደ ቀይ አበባ

ጽጌ የተባልሽ ማርያም ሆይ! ከንፈሮችሽ እንደ ፍሕሶ አበባ ቀዮች ናቸው፤
መሠዊያ ማጎፀንሽም በአበባ የታጠረ ነው፤
የሕይወቴ ምልክት ድንግል የቤተ መንግሥት አበባ ሆይ፤
የንጽሕናሽን የፍቅር አበባ ተቀዳጅቼ፤
አንቺን አበባዬን በማጎሌተ ጽጌ አመሰግንሻለሁ።

8. የምልክት ወተት ያፈሳል

ከነጫጭ ጥርሶችሽ የተአምር ወተት ይፈሳል፤
ከከንፈሮችሽም መልካም የማር ወለላ፤
ፍሬ የምታስገኝ ማርያም አበባ ሆይ!፤
ሽታዬን በመልካም ሽቶሽ ለውጭ፤
አልጫነቴንም በፍቅርሽ ጨው አጣፍጭ።

9. የፊትሽ ደምግባት

ማርያም ሆይ የፊትሽ ውበት እንደሮማን አበበ ቀላ፤
በልቤ ውስጥም ደስታን ጨመረ፤
ከወይንና ከሥንዴ ፍሬ ይልቅ ተአምርሽ በዛ፤
ቁርየ ጸራቅሊጦስም የመከር ጊዜ ደረሰ ብሎ፤
በአንደበቱ አሰምቶ ተናገረ።

10. ገነትሽ አነፈሰ

ተስፋ ባላቸው ሕዝብ አፍ የምስጋናሽ ሽቶ ይፈስ ዘንድ፤
የተክል ቦታ ገነትሽ ቦኦ መዓዛ የተሸከመ የደቡብ ነፋስን አነፈሰ፤
ለተአምርሽም ደስታ በሚደረግበት ቦታ፤
ኪሩብ በክንፉ ስዕልሽን ሲጋርድ፤
ብልሀዋ የእስራኤል ድንግል ሆይ ወደ እኛ ደጋግመሽ ነይ።

11. እነሆ አበበ

ምእመንን የሚባርክ ተአምርሽ ናርዶስ፤
እነሆ አበበ መዓዛንም ሰጠ፤
መርዟ ከሚገድል ከአውሬ እህት ከኃጢአት ወጥመድ፤
እንደ ሰላ ግልገል እንደዋልያም ደቦል! ሩጪ አመልጥ ዘንድ፤
ማርያም ሆይ በመዓዛው የመዳን መንገድን አመልክችኝ።

12. ወደ ወይን ቤት አስገቡኝ

ድንግል ሆይ ተአምርሽና ምስጋናሽ በአንድነት፤
ወደ ወይን ቤት አስገቡኝ በዚያም በፍቅር አስተናገዱኝ፤
አንድ ጊዜም በሽቱ አጽናኑኝ፤
የአበባሽ አካል ሙሽሪት መታሰቢያ ስታደርግ፤
በኋላም በእንኮይ ኮሉኝ (አሸቡኝም) አለች።

13. ተነሥተሽ ነይ

የገነት ወፍ ሆይ ከሽቱ ተራሮች ተነሥተሽ ነይ፤
በየአቅጣጫው ያሉ ምእመናንንም ጐብኚ፤
ተአምርሽ የሚወደድ የትንቢት ርግብ ማርያም ሆይ፤
ክንፍሽ በነጭ ብር የተጌጠ ነው፤
ጐንሽም በአረንጓዴ ወርቅ የተሸለመ ነው።

14. ሙሽራ እንደሚደሰት

አበቦችን ያይ ዘንድ በወደደ ጊዜ ወደተክል፤
ቦታው የወረደ ሙሽራ እንደሚደሰት፤
ከኃጥአን ጫንቃ ከባድ የኀዘን ቀንበርን የሚያቃልል፤
ከአንቺ ታላቅ ደስታ ተወልዷልና፤
ድንግል ሆይ! በተአምርሽ እጅግ እደሰታለሁ።

15. ሰላምን የምትሰጭ

ለላምን የምትሰጭ ድንግል ሆይ! ከሩቅ ታበሪያለሽ፤
በደብረ ምጥማቅም ለሁሉ ትገለጫለሽ፤
ኃጢአተኛውን ለማዳን ከብርና ከወርቅ ይልቅ የሚጠቅም፤
የተአምርሽ የጽድቅ ቃል በምድራችን ተሰምቷልና፤
የበረሓ አበባ ቁርየ[1] ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ።

16. በአዳምና በሔዋን በደል

በአዳምና በሔዋን በደል ሱራፊ መልአክ የዘጋትን
የገነትን በር፤
ያለ ጽድቅ አበባሽ የከፈታት ማን ነው፤
በተአምርሽ ወደ ገነት ገብታ፤
ሔዋን እንደ እንቦሳ ዘላለችና፤
አዳምን ከምርኮ ያስመለሽ ድንግል ደስ ይበልሽ።

17. ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ

ከሥላሴ አንዱን (ወልድን) የወለድሽልን፤
ወንድ የማታውቂ ድንግል ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ፤
የሙሴ እኅት ማርያምም
በኤፍሬምና በምናሴ ወገን ፊት ከበሮ እየመታች
ለተአምርሽ ምስጋና አቀረበች።

[1] ቁርየ በዓመት አንድ ጊዜ በጥቅምት ወር ብቻ የሚታይ ደስታ አብሣሪ ድምፀ መልካም የሆነ የአእዋፍ ዘር ነው።

18. ብትኖሞ ሆይ! ደስ ይበልሽ

ለኃጥአን ነፍስ ይቅርታ የሚያደርግ ወልድ ዋሕድን
ወልደሽልናልና፤
ምሳሌ የሌለሽ ብቸኛዋ ሆይ! ደስ ይበልሽ፤
ማርያም ሆይ! ከፍ ብሎ ሰማይ ያመሰግንሻል፤
የፍቅርሽን አበባ /ጽጌ/ አክሊል አድርጋ፤
ምድርም በዓል ታከብራለች።

19. ቀስተ ደመና ማርያም ሆይ!

እግዚአብሔር ለምሕረትና ለፍርድ መታሰቢያ የሾመሽ፤
የኖኅ የቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተ ደመና ማርያም ሆይ!፤
ምድርን ስለ ቀሰፉት፣ በጥፋት ውኃም ስለመታት፤
ሰማይን በከዋክብት እንደሸለመው፤
በአንቺ ምልጃ ፍሬ በሚያስገኝ አበባ ሸለማት።

20. የተባረኩብሽ የተቀደሱብሽ

አሕዛብ የተባረኩብሽ የተቀደሱብሽ፤
የአባት አብርሃምና የዛሩ ምልክት፣
የድንግልና ልጅሽ /አበባ/ ለይሳሐቅ ቤዛ የተሰጠ፤
የያዕቆብ መውጫ (ምሥራቅ) ዕፀ ሳቤቅ ማርያም ሆይ!፤
የአጥቢያ ኮከብ የተባለ ያአምላክ እናት ነሽ።

21. መጽሐፍ እንደተናገረ

መጽሐፍ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል፣
ለአረፍት የተሾምሽ የቃል ኪዳን ምልክት ነሽ ብሎ
እንደተነገረ፣
የሰንበታት ሰንበት የብርሃን ቀን ማርያም ሆይ፤
አበባ ያላት የገነት ጻድቃን በአንቺ ይደሰታሉ፤
ኃጥአንም በአንቺ ከደይን ይወጣሉ።

22. ነቢያት አሱሽ

ቡትጃት መንፈስ አስቀድመው ሥውር ምሥጢርን ያዩ ነቢያት፤
የተዘጋች የተክል ቦታ፣ የተቆለፈች የምሥራቅ በር ነሽ አሉሽ፤
ድንግል ሆይ!እንደምትፀንሽ ወንድ ልጅንም እንደምትወልጅ፤
እግዚአብሔር አስቀድሞ ለዳዊት ወገን ምልክትን ሰጠ፤
ኢሳይያስም ግልጽ ትንቢትን ተናገረ።

23. ማርያም ሆይ! ተአምርሽ

ዕፀጳጦስ ሁነሽ ከመለኮት ጋራ በተስማማሽ ጊዜ፤
ማርያም ሆይ ተአምርሽ በኦሪት ተሰበከ ተነገረ፤
ሊቀ ነቢያት ሙሴ ያየሽ ያለመለምሽ ድንግል፤
እሳት ልጅሽ የኃጢአቴን እሾህ ሊያቃጥል፤
በለመለመ ቅርንጫፎችሽ ጠብቂኝ።

24. የአሮን በትር ማርያም

ላይተክሏት የበቀለች፣ የለመለመች፤
ውኃ ሳያጠጧት ያበበች፣ ያፈራች፣
የአሮን በትር ማርያም ሆይ! ተአምር አሳየሽ፤
ስለዚህም ጥዑመ ልሳን ያሬድ፤
የወንጌል አጥር ይከባታል፤ ጽጌረዳም በመስቀል አምሳል
ብሎ ከሱራፌል ጋራ አመሰገነሽ።

25. ውበትሽ አበበ

በካህኑ በአሮን ልብስ ውበትሽ አበበ፤
ድንግል ሆይ! ድንግል ምድር ባስገኘችው ተአምርሽም፤
በሮማን አበባ አምሳል ወርቅ አፈራ፤
እውነተኛ ወርቅ ጸናጽልሽ (ሺሺቴ) ግን፤
ከወይን ማስደሰት ይልቅ የገድሉ ጣም የሚያስደስት
ፈቅጦር ነው።

26. የትንቢት አዝመራ

የትንቢት አዝመራ ማርያም ሆይ የአዲስ አበባ ዘመን ነሽ፤
የረኃብ ዓመት ለውጥም ዘመነ ጥጋብ ነውና የፍሬ ዘመን ነሽ፤
ከይሁዳ ተራሮችና ኮረብቶች የመዓር ወለላ ነጭ ወተትም
ይፈሳል ብሎ፤
ነቢዩ ኢዩኤል የተናገረው በአንቺ ታወቀ ተፈጸመ።

27. ዘካርያስ አየ

የብርሃን ተስፋው ወርቅ ጽዮን ማርያም ሆይ፤
ካህኑ ዘካርያስ በየካቲት ወር መባቻ፤
በሁለት የዘይት ቅርንጫፎች መካከል ተአምርሽን አየ፤
እዝራም በምድረ በዳ ወድቆ /በጸሎት/ በዋለ ጊዜ፤
የፊተኛ ህብር እንደ አበባ ፍካት ተገለጠለት።

28. ንዑዳን ክቡራን ኃጥኣን

በገድሉ ዋጋ ከሚመካ ከጻድቅ እስጢፋኖ ይልቅ፤
በተአምርሽ የሚታመኑ ኃጥኣን ብዑዓን ናቸው፤
የመለኮት አበባ አካል የሆንሽ ድንግል ሆይ ያለ አንቺ፤
ዓለምን ሁሉ ማዳንንስ ተይውና፤
ነቢያት እንኪን ነፍሳቸውን ከኩነኔ ማዳን አልቻሉም።

29. የማን ፍቅር

የውበት አምሳያ ከሌለው አበባ ፍቅርሽ በሰተቀር፤
እግዚአብሔርን ከሰማይ የማን ፍቅር ሳበው፤
ለሞት እስኪደርስስ የማን ፍቅር ወደ ምድር ሳበው፤
ማርያም ሆይ! ይህን አስቦ ይህንም ጠብቆ፤
ለተአምርሽ ዕልልታን የሚያውቅ ምስጋናንም የሚያቀርብ
ብዑዕ ነው።

30. ወይንና ዘፈን

ወይንና ዘፈን ልብን ያስደስታሉ፤
ነገር ግን ከሁለቱም ይልቅ ምስጋናሽን መናገር ያስደስታል፤
ርኩሰት የሌለብሽ ድንግል ሆይ!፤
ንግግርን አጣጥመው ተአምርሽን ያመሰግኑ ዘንድ፤
የጌታየ እናት ከሹቶችሽ ወተት ከንፈሮቼን ቀቢያቸው።

31. በመጠጥ ቤት

በመጣሆን ቤት የመሰንቆና የማኔሌተ ገጸ ምስጋና እጅግ ጥሩ ነው፤
ከእነሱ ይልቅ ለተረዳ ሰው ምስጋናሽን መስማት እጅግ በጣም ጥሩ ነው፤
ለኃጢአተኛው ጽድቁን ያስገኘሽለት ማርያም ሆይ!፤
ተአምርሽ ድንቅ ነው ነፍሴም ትረዳዋለች፤
ብዛቱን ለመጻፍ ግን መቁጠር አልችልም።

32. ወይን ለማይጠጣ

"ሂራክ የልብ ደስታ ነውና
ወይን ለማይጠጣ ሰው ሕይወቱ ምንድን ነው? አለ
ማርያም ሆይ ከዚህ የሚጥም ተአምርሽን፣
የውበት እይታው የሚያስደስት የፍቅርሽን ምስጋና አበባንም
በመናቅ ለሚያታልል ሰው ግን ሕይወት የለውም።

33. ሚልኮል አስከትንቀው

እንቺን በአብራኩ ያስገኘ የእሰራኤል ንጉሥ ዳዊት፤
ሚልኮል አስከትንቀው በታቦቱ ፊት እንዳመሰገነ፤
ድንግል! እኔም በሥዕልሽ ፊት አብዝቼ አመሰግናለሁ፤
ተአምርሽንና ቁርባን ምሰጋናሽንም የሚንቅ ሰው ቢኖር፤
በስውና በመላእክት አንደበት የተናቀ ይሁን።

34. በሚንቀለቀል ሰይፍ

በሚንቀለቀል የእሳት ሰይፍ ሱራፌ መልአክ የሚጠብቅሽ፤
ጸሐፌ ሄኖክም መዓዛ ቅድስናሽን ያሸተተ፤
የማትረግፊ የገነት አበባ ማርያም ሆይ፤
ተአምርሽን ዘወትር አመሰግን ዘንድ በኃይለኛ ቀላፌ መልአክ እጅ፤
የጠላቴን አራስ እንደሚረግፍ አበባ ፈጥነሽ አርግፊ።

35. ጻድቅ እንደሚደሰት

አሪታዊ ጻድቅ በቀልን ባየ ጊዜ እንደሚደሰት፤
ጠላትን በመበቀል የተአምርሽን ኃይል ግለጭ /አሳይ፤
የእመአምላክ እናት ሆይ! አንቺን የጠፋ እንደኋት ቤኪይውት ይኖራል?፤
በእናትና አባቱ ላይ የስድብ ቃል የተናገረ፤
በልጅሽ ፍርድ ይመት ተብሎ አይደለምን?።

36. ማርያም ዝምታሽ

ማርያም ሆይ! ወንኖችሽ የተአምርሽን ሥራ አስክናይ ድረስ፤
ዝምታሽ ከማድነት አለፈ፤
የተክል ቦታሽ ሰላምና መፋቀርን ታብብ ዘንድ፤
የወይን ቦታ መሰማሪያችንን የሚያጠፉ፤
ጥቃትን የቀበሮ መንጋዎችን ፈጥነሽ አጥምጂ።

37. በጉ የመንግሥት ምሥጢር

ማርያም ሆይ መልአኩ ሩፋኤል ለጦቢት እንደ ነገረው፤
በጉ የመንግሥት ምሥጢርን ለመሰወር፣
የልጅሽን ሥራም በክብር በመግለጥ ፈንታ ቅንዓት ይዞታልና፤
ተአምርሽን በሸፍጥ የሚሰውረውን (የሚደፍነውን)፤
ቀደሞ ዳታንን እንደደፈነችው ምድር በሕይወቱ ትድፈነው።

38. እወድሻለሁ የሚል ግን

እወድሻለሁ የሚል ተአምርሽን ግን የማይወድ ክርስቲያን፤
ክርስቲያን አይደለም፤ አይሁዳዊ፣ የሐሰተኛ እስጢፋ ቡቃያ ነው እንጂ፤
ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት የተወለድሽ እመቤቴ እኔ ግን አልሁ፤
ሙሽራሽ አበባ ሙሽሪቱን እንደሚወድ፤
በዳዊት ልጅ በሰሎሞን ምስጋና ደስታሽን እወደዋለሁ።

39. ከወገንሽ ልጆች እኔ

ከወገኖችሽ ልጆች እኔ ድሀና በደለኛ ስሆን፤
የኃጥአንን በደል የሚደመስስ ተአምርሽ፤
ሁሉን የሚመግብ አበባሽ የሀብት መዝገብም አለኝና፤
ድንግል በአንቺ ባለጠግነት እንደ ንጉሥ እመካለሁ፤
በጽድቅሽም እንደ ጻድቅ ሰው እደሰታለሁ።

40. በጐ መዓዛሽ ሸተተኝ

የተክል ቦታ መዓዛ ከሩቅ መንገድ እንደሚሸት፤
ነፋሳት ሲነፍሱ በጐ መዓዛሽ ከሩቅ ሸተተኝ፤
የተቀመመ የሽቶ መዓዛ ያለሽ የቤተ መንግሥት አበባ ማርያም ሆይ!፤
የተባረክሽ የሰሎሞንና የዳዊት የዘውድ አበባ ነሽ፤
የአሮንም የክህነቱ የአክሊል አበባ ነሽ።

41. ማርያም ሆይ! የደስታ ተአምር

የሚያስደስት ተአምር ያለሽ የተድላ የደስታ አበባ ማርያም ሆይ፤
የምስጋናሽ መዓዛ ምድርና ሰማያት ሞላ፤
በምስጋናሽም ጠላትን ያቸነፉ ሁሉ፤
ብርሃናዊ መጽሐፍንና ረቂቅ መና ይቀበላልና፤
በፍቅርሽ ማኅሌት አቸንፍ ዘንድ ጽናቱን አስታጥቂኝ።

42. የገነት ምድር ሳትፈጠር

የገነት ምድር ሳትመሠረት የአበቦችም ውበት ሳይታይ፤
ጠቃሚ ተአምርሽ በሥላሴ ሐሊና ነበረ፤
የአሸናፊ **አምላክ እናት** አሸናፊቱ **ማርያም** ሆይ!፤
ሕዝብሽን የሚገፋ ጠላትን ታጠፊ ዘንድ፤
ከኤርሞን ተራራ ራስ ነይ ነይ ነይ።

43. አብቤ

እኔ አላፊው የኪሩቤልን (ልሳን) አንደበት አብቤ (አንደበቴ አድረጌ)፤
ምስጋናሽን በመናገር ባልፈጽምም እንኳን፤
ነገር ግን **ማርያም** ሆይ! የተሸከመችሽን ማኅፀን አመሰግናለሁ፤
መድኃኒት የሆንሽ አንቺን ፀንሳ ሳለች፤
የሚዳስሷትን በሽተኞች ሁሉ ትፈውስ ነበር።

44. ምንኛ የተከበረች፣ የተቀደሰች

ሐና አንቺን ያበበችባት፤
ሚች **ኢያቄምም** አንቺን ለሕይወት ያፈራባት የደስታ ለዓት፤
ምንኛ የተባረከች፣ የተቀደሰች ናት፤
የዓለሙ ሁሉ መድኃኒት አንቺ ነሽና፤
አንዲት ርግቤ ሆይ! ተአምርሽን አመሰግናለሁ።

45. የባልቴቱ ሰርግ መፀነስሽ ነው

የእግዚአብሔር ሕዝብ ጮልምስና የታደሰብሽ ሆይ!፤
የሽማግሌውና የአሮጊቲቱ ሰርጋቸው መፀነስሽ ነው፤
የወይን ተክሎች የጸጋ ፍሬ አንቺን አፈሩ፤
ትርንጐምችም በጐ መዓዛን ሰጡ ያለው ነቢይ፤
የሐና አበባ ሆይ! ማኅሌተ ጽጌን ያነቡ ዘንድ አመለከተልሽ።

46. የነገሥታት ንጉሥ ሰሎሞን

ሙሽሪት ሆይ ከትንቢት አንበሳ ጉድጓድ በወጣሽ ቀን፤
የነገሥታት ንጉሥ የሰሎሞን ልብ እንደተደሰተ፤
የሐና አበባ ሆይ በደስተኞች ማኅበር መካከል፤
ተአምርሽን እየተናገርኩ አመሰግንሻለሁ፤
እንደሚጠባ እንቦሳም በማስተዋል ጐዳና እዘላለሁ።

47. ምድር ተቀደሰች

በለሶች ለምልመው አንቺን በአበቡ ቀን፤
ምድር ተደሰተች፤ ሰማይም ዘለለ፤
ወደር የሌለሽ የሕይወት ተአምር ማርያም ሆይ!፤
መልአከ ሞት እስኪፈራ፤ ሰይጣንም እስኪደነግጥ፤
የልደትሽ ዜና ነጐድጓድ በሲያል ተሰማ።

48. ማርያም ሆይ! የመወለድሽ ዜና

በኤፍራታ የሰማሁትን የመወለድሽን ዜና፤
እነሆ በመንታ ዛፎች ሥር አገኘሁት፤
በሁለቱ ጡቶቿ ወተት በውስጧ ባለ ተአምርሽም፤
በመልካሙ ሽቱ ድኃ አደጉን ታሳድጊኝ ዘንድ፤
ማርያም ሆይ! ወደ እናትሽ ቤት አስገቢኝ።

49. ማርያም ሆይ! እናትሽ ትመስላለች

ማርያም ሆይ እናትሽ ሐና አበባን ያስገኘች ዕለተ ማክሰኞን፣

ብሩህ ፀሐይን ያስገኘች ዕለተ ረቡን ትመስላለች፤
በሰማይና በምድር ላሉ ዕረፍት የሆንሽ፤
የነፃነት ቀን ዕለተ ሰንበት አንቺን በተአምር አፍርታለችና፤
ዳግመኛም ሰባተኛን ቀን ትመስላለች።

50. የተፈጸመ ድኅነት ምንድር ነው

ድንግል! አንቺ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት ሳትወለጂ፤

የተፈጸመ ድኅነት ምንድር ነው?

ሥጋና ነፍስሽን የተዋሐደ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ሆነ፤
ዮሐንስ በማኅፀን ለልጅሽ እንደሰገደ፤
እኔም በነፍስና በሥጋ አብራክ ለተአምርሽ እሰግዳለሁ።

ማኅ ♦♦♦

ክፍል ሁለት

51. እንደ ሰዶም በሆነ

ኃጥኣንን ለንስሓ ልጠራ መጣሁ እንጂ፤
ጻድቃንን ለመጥራት አልመጣሁም ብሎ፤
የሰበከ መድኃኔዓለምን ያስገኘሽልን የተአምር ሥልጣን ያለሽ ማርያም ሆይ!፤
እግዚአብሔር አንቺን ባያስቀርልን፤
እንደሰዶም በሆንን፣ ጐሞራንም በመሰልን ነበር።

52. ቁልቁል ቢሰቀል

ቁልቁል ቢሰቀል፣ በራሱም ቢተከል፤
ያለ አንቺ ረዳትነት ነፍሱን ማዳን የሚችል የለም፤
ድንግል ሆይ ስድስቱ ቃላትን በመፈጸም አይደለም፤
የተአምርሽ ሞገስ ይደነቅ ዘንድ፤
ከአንቺ ጋር እንዲመላለስ በአበባ ቦታ ሹሚኝ እንጂ።

53. በወርቅ እንደተለበጠች ታቦት

ማርያም ሆይ! በዐረብና በተርሴስ ወርቅ እንደተለበጠች ታቦት፤
በነፍስና በሥጋ በድንግልና የተለበጥሽ ነሽ፤
ኢያቄምና ሐና ቀንሞስና ቀናንሞስ፤
መለኮት የጠበቀሽን አንቺን በሦስት ዓመት ከአስገኙ በኋላ፤
በቤተ መቅደስ መኖር ተአምርን አሳየሽ።

54. ጠፍ ለመኖሪያዋ ቤት አገኘች

ወፍ ለመኖሪያዋ ቤት አገኘች እያልኩ፤
በዳዊት መዘሙር አመሰግንሻለሁ፤
ማርያም ሆይ! የምስጋና ሕግን የምታብብ ተአምርሽ፤
በየጊዜው ፍሬ እንደ ምትሰጥ፤
በውኃ ምንጭ ዳርም እንደተተከለች ተክል ትመስላለች።

55. ማርያም ሆይ! ያገኘሽ ያለ እናት ማደግ ያሳዘነኛል

ማርያም ሆይ! የሐናን ጡት እየጠባሽ ወደ ቤተ መቅደስ በገባሽ ጊዜ፤
ያገኘሽ ያለ እናት ማደግ ያሳዘነኛል፤
ዳግመኛም በደመና የሚጫን የእሳት አበባ የለበሰ ሩኑኤል፤
እንደአባት ከመላእክት ጋራ መና እየመገበሽ፤
በቅድስና የማደግሽ ምሥጢር ያስደስተኛል።

56. ፈትለሽ አልደከመሽም

መንፈስ ቅዱስ የሸመነው የንጽሕና ልብስ አለሽና፤
የጌጥ ልብስ ለመልበስ ፈትል ፈትለሽ አልደከምሽም፤
በአዲስ ዘመን ሁሉ የምትታይ ማርያም አበባ ሆይ፤
ከውበትሽስ ይቅርና ከአበቦች እንደ አንዲቱ እንኳን፤
በንግሥና ዘመኑ ሁሉ ንጉሥ ሰሎሞን አለበሰም።

57. ከመጽሐፍ የተከል ቦታ እቀሰማለሁ

ንብ ማር ለመስራት አበባ እንደሚቀስም፤
ከመጽሐፍ የተከል ቦታ ተአምርሽን ለመናገር እቀስማለሁ፤
የተጠማውን ውሻ በጫማሽ ውኃ ያጠጣሽ፤
በጭንቀኛ የመጠማት ጊዜ ከሮማንሽ ምንጭ ታጠጭኝ ዘንድ፤
የዋሂት ርግብ ማርያም ሆይ! ራሪልኝ።

58. በምድር እንዳለ ጽጌረዳ

ማርያም ሆይ! ከበጐ መዓዛና ከቅላት ጋር በምድር እንዳለ ጽጌ ረዳ፣
ከብርሃንና ከሙቀት ጋር በሰማይ እንዳለ ፀሐይ፤
በሁሉም ቦታ አግኝቼ አይሽ ዘንድ፤
ከተአምርሽ ምንጭ ሽቱ ወደሚቀዳበት፤
አሳጭኝ ዐይኖችሽ ይጥቀሱኝ።

59. ፀሐይ ከቆመ ዘንድ

የገሊላ አበበ ማርያም ሆይ!፤
በጨረቃ ግብዓት መካከል ፀሐይ ከቆመ ዘንድ፤
ሳቤላ አይኗን ወደ ሰማይ አቅንታ፤
በታናሽ ድንግል ብላቴና አምላል፤
ከጨረቃ የሚደምቅ ሕፃን ልጅ ታቅፋ ተአምርሽን ተመለከተች።

60. እግዚአብሔር ሁሉንም ዓለም ተመለከተ

እግዚአብሔር ሁሉንም ዓለም ተመለከተ!
ማርያም ሆይ! እንዳንቺ ያለች እናት ግን አላገኘም!
ከማኅፀንሽ የተቀለመ አበባ እሱን ግን!
ንጉሥ ውብ ደም ግባትሽን ወዷልና!
ልጅ ሆይ! ለሚ ዳግመኛም አድምጭ በማለት፤
አባትሽ ዳዊት አስቀድሞ አመለከተሽ።

61. ማርያም ሆይ! የፍቅርሽ ምስጋና

ምላሌሽ የሚሆን ግምጃን ከዘረጋ ዘንድ፤
ጌዴዎን አወራረዱን የተመለከተው የብሱን የሚያረጥብ፤
ባሕሩን የሚያደርቅ፣ የረድኤት ምልክት (ጠል) አለሽና፤
ማርያም ሆይ! የፍቅርሽ ምስጋና በሰው ሁሉ፤
አንደበት ሁል ጊዜ ያብባል ድርቅም አይፈራም።

62. የወርቅና የሐር ፈትል

የብርሃን ተአምር ያለሽ ማርያም ሆይ!፤
ሕፀፅ በሌለባቸው በመለኮትና በሥጋ አምላል፤
[2]የወርቅና ሐር ፈትል በጣቶችሽ ሲስማሙ፤
በጐ የምስራች የያዘ የገብርኤልን ድምፅ ለምተሽ፤
የጽድቅ ፀሐይ ጌታን ያለ አባት ፀነስሽው።

[2] ወርቅና ሐሩን እያለማማሽ ስትፈትዩ ሄኖ

63. የተአምር ምስጋና ታሳቅ ነው

የተአምር ምስጋናን በድንግልና ማበብሸ፤
የሚያለመልም የአምልኮ ቁርባንንም በንጽሕና ማፍራትሽ
እውብ ድንቅ ነው፤
ማርያም ሆይ! ያለ አንቺ ምልጃ በሱራፌል የወርቅ
ማጠኛ በኪሩቤልም የእንቁ ጽዋ የሚያርግ፤
ጸሎትም የለም፤ ምልጃም የለም።

64. ምን ይደንቅ

በአንቺ እቅፍ አምላል፤
የተሣለ የሕፃን መልክ ያለበት ትንቢት የተነገረበት ኳብ ምን ይደንቅ?
ድንግል ሆይ! ተአምርሽን ይገልጥ ዘንድ በጊዜ ወጣ፤
የጥበብ ሰዎችንም ከሩቅ ከአውራጃ፤
ልጅሽ ተኝቶ ወደ አለበት በረት አደረሳቸው።

65. ልጅሽን ታቅፈሽ

በመንጻት ወራት፣ በተአምርም ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ስትገቢ፤
ነጭ እና ቀይ አበባ የሚመስል ልጅሽን ታቅፈሽ፤
ከንዘኔ ታረጋጊኝ /ታጽናኚኝ ዘንድ ርግቤ ሆይ ነይ፤
መልካም እናቴ ሆይ ደስ የሚል ዜና ከያዘ ከገብርኤልና፤
እንደ አንቺ ርኅሩኅ ከሆነ ኮሚካኤልም ጋራ ነይ።

66. አመሬ በተከታተለሽ ጊዜ

ልጅሽን ለመብላት ያሰበ አውሬ በተከታተለሽ ጊዜ፤
ወደዱር ወጥተሽ ፈጥነሽ ስትሸሽ፤
ለዮሐኒ ክንፍ እንደተሰጠው ክንፍ የተሰጠሽ፤
ፀሐይ ለብሰሽ በሰማይ የታየሽ ሴት ማርያም ሆይ!፤
በራእይ ያየ ዮሐንስ ተአምርሽን ጻፈ።

67. የመገፋት ተአምርሽን ለማሳየት

እመቤቴ ማርያም ሆይ!፤
ከሰይጣን ከሄሮድስ ፊት የመገፋት ተአምርሽን ለማሳየት በሸሸ ጊዜ፤
ከለመለሙ የልጅሽ እግሮች ጋር በመንገድ የደከሙ እግሮችሽ ከቆሙ ዘንድ፤
ቁስቋም የተባለች ቅድስት ገዳምሽን፤
በእግር ደርሼ በስግደት በተሳለምኳት በወደድኩ ነበር።

68. የሮማን ሽቱ ማርያም ሆይ!

የቀናንሞና የአበሜ አበባ የሮማን ሽቱ ማርያም ሆይ!፤
የመልክሽ ልምላሜ በጾም እስኪጠወልግ፤
በችግር ጊዜ የደረሰብሽን የልቅሶና ስደት ተአምር፤
ፍጻሜ የሌለው ደስታሽንም፤
እንደ ሰሎሜ እንደ እኅትሽ በተሳተፍኩ በወደድኩ ነበር።

69. እኔ የቤትሽ ተክል ጠመሰግሁ

እንቺ የመንግሥት አበባ በረታበኝ በሃነም ሐሩር እንያጠወለግሽ፤
እኔ የቤትሽ ተክል በኃጢአት የበጋ ነፋስ ጠመለግሁ፤
ማርያም ሆይ ሽቱ በሚያብብበትና በሚያፈራበት፤
በፅንሳሽ እርጭኝ፤
በበልግ ተአምርሽም ጽድቅን እንዳብብ አድርጊኝ።

70. የቁስቋም ነጋዴዎች ለእንስሳ

የቁስቋም ነጋዴዎች በመንገድ የጋለቧቸውን እንስሳት፤
የበረከት ቅብዐትን ትቀቢ ዘንድ እግራቸውን ያላቀለልሽ፤
ተአምር ያለሽ ሙሽሪት ሆይ! አበባሽን ቅብዐት ቅቢኝ፤
ለፍጥረት ሁሉ የምትራሪ ነሽና፤
ማርያም ሆይ! በጉንትሽ ለሰው ብቻ አይደለም።

71. ወደ መርከቡ ስትገቢ

ለምለም የወይራ ቅጠል ይዘሽ ወደ መርከቡ ስትገቢ፤
ለኖኅ የይቅርታ ጊዜን በምልክት እንዳበሰርሽው፤
ለእኔም የፊካ አበባ ይዘሽ ጽድቅን አብስሪኝ፤
ክንፎችሽ መስቀል የሆኑ የቁስቋም ርግብ ማርያም ሆይ!፤
እግዚአብሔር ይመስገን ከንዘን ወደ ደስታ መሸጋገሪያዬ ነሽ።

72. ድንግል ብዙዎች

እመቤቴ! የልጅሽን ተአምር የፈለጉ ብዙዎች፤
አመስግነው ሁሉን አልጨረሱምና፤
በቅብዐ ሜሮን የታተመች ቤተመቅደሱ፤
የደረቁ የዮሴፍን በትሮች ተክሎ ካለመለመና ካላበበ ዘንድ፤
ወልድ ወንድሜ በብላቴናነቱ ጊዜ ከአርያም፤
ወርዶ ከልብሱ ሽቱ አፈሰሰ በማለት አመሰገነች።

73. ድንግል ሆይ! ስንቱን

ድንግል ሆይ! የልጅሽን ተአምራት ስንቱን እናገራለሁ?፤
በስምዖን ጴጥሮስ አጠገብ በተቀመጠ ጊዜ ትሕትናውንም
ስንቱን አስባለሁ?፤
በዮሐንስ ፊት አጐንብሶ እንደቆመ ነውን?፤
ወይም በደብረታቦር ብርሃኑ እንደተገለጠ፤
በደም ግባቱም ሰማያትን እንደጋረደ።

74. በሰንቺ በዮርዳኖስ

እመቤቴ! በአንቺ፣ በዮርዳኖስም፣ በደብረ ታቦርም፤
በሦስትነቱ መጨመርም መቀነስም ላይኖርበት፤
ሰለው ልጅ ሁሉ የአካል ሦስትነቱን ያሳይ ዘንድ፤
ድንግል! ልጅሽ ተአምሩን ሦስት ጊዜ ገለጠ፤
በብርሃኑም ጨለማን አበራ።

75. በወድሰ ሞት ምልክት

ወልድሽ ሞት ምልክት ዓለም ፈጹማን ከሰበሰ ቦኋላ፤
ወደ መቃብሩ በሰቅሶ ገሥግሠሽ፤
ብርሃንን ተጐናጽፎ ባየሽው ጊዜ፤
ልጄ! በእውነት ተነሣህን አልሽው፤
ቁርባን አፉንም በአፍሽ ሳምሽው።

76. ስንት ነፍሳትን

መዋጥ ከለመዱ ከሞትና ከሲኦል አፍ፤
የተአምርሽ ኃይል ስንት የሰው ነፍሳትን ነጠቀ(አዳነ)፤
ጸዊት አባትሽም መንፈስ ቅዱስ በትንቢት ገልጾለት፤
ምርኳችንን የመለሰ ልጅሽ የነሐሱን በር ሰበረ፤
የብረቱንም መቸንከሪያ ቀጠቀጠ ብሎ ያን ጊዜ የትሣኤን
መሰንቆ ደረደረ።

77. ማርያም ሆይ! ምልክት ይረዳ ዘንድ

ማርያም ሆይ! የልጅሽን ምልክት ይረዳ ዘንድ በድንግልና
መወለዱን፤
ወደ መቃብር መውረዱንና ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን፤
ወደ ሰማያት ማረጉንና፤
በመቃብሩም በየቀኑ ብርሃን መውረዱን ሰምቶ የማያምን
ሰው ቢኖር፤
ይመለስ፤ የተናገረውን ከንቱ ነገርም ያስተውል።

78. የደመና አበባ ማርያም ሆይ!

የደመና አበባ ማርያም ሆይ! ሥጋሽን የተዋሐደ ወልድ፤
የማሸነፍ ምልክት ምርኮን ከሲያል ወሰዶ፤
ወደስጓን ኮረብታ ወደ ከርቤ ተራራም በወጣ ጊዜ፤
መኳንንት ለክብር ንጉሥ ደጅ ከፊቱ የሚል፤
የሥልጣን ቃል /መለከት/ ተሰማ፤ እልልታም ተመመ።

79. የኤርምያስ ጥዑም መዓዛ

የኤርምያስ ጥዑም መዓዛ የማጎፀንሽ አበባ ሕብስተ ሕይወት ወልድ፤
በልዩ የተአምር መዓዛ ወደሰማይ በነጠቀሽ (ባሳረገሽ) ጊዜ፤
መብረቅ የታጠቁ መላእክት በክብር ተቀበሉሽ፤
ንግሥቲቱን አንቺን ወደ ብርሃን ድንኳን እስክስገቡሽ ድረስም፤
ከበሮ የሚመታ አለ፣ እንቢልታም የሚነፋ አለ።

80. እግዚአብሔር በትንቢት ቃል

እግዚአብሔር በትንቢት ቃል የእኛ የሆነ ሥጋሽን ለብሶ፤
በምድር በተገለጠ ጊዜ፣ ለእኛም ሲታይልን፤
የባሕሪያችን መመኪያ ሆይ!፤
በሰማይ መገለጥ ሆነ፤
ዛሬ ለማርያም ለእናታችን ደስታ ይገባል እያልን
እናመሰግንሻለን።

81. ወደሌላ ሀገር ከፈለስኩ ዘንድ

ሀገሬን ትቼ ወደ ሌላ ሀገር ከሄድኩ ዘንድ፤
ድንግል ሆይ! የአርባ ቀን ምስጋናሽ መዘመር ሆነኝ፤
ማርያም ሆይ ተአምርሽ እንደተናገረ፤
ጌቴሴማን መቃብርሽ መርከብ ስትሆን፤
የእሳት ባሕርን ታሻግሪኝ ዘንድ ውደጂ።

82. ከኤዶም በወሰዱሽ ጊዜ

ድንግል ሆይ! አእላፍ መላእክት በየነገዱ፤
በመባርቅ አክናፍ እንደጋሻ ጋርደው ከኤዶም በወሰዱሽ ጊዜ፤
የሰማይ ሠራዊት- ምርማ ምልክት ለተሰጣት ለፍልሰትሽ
ኾዘር፤
አወጣጧ ከምድረ በዳ አበቦች መሐል የሆነ፤
እጥናቷም እንደሰኒን ጪስ አወጣጥ ልብ የሚመስጥ፤
ያቺ ማናት እያሉ አመሰገኑሽ።

83. በእቅፉ ይዞሽ

ወልድ በእቅፉ ይዞሽ በአፉም እየሳመሽ፤
በቀኙ እቅፍ ሊያሳርፍሽ በወሰደሽ ጊዜ፤
በጐ መዓዛ ያለሽ የጎነት አበባ ማርያም ሆይ!፤
ከንፋቸውን እያማሉ፤
ይቀበሉሽ ዘንድ መላእክት ወረዱ።

84. ከአበባ በምድር የመፋለስሽ ምልክት

በሁለት መንን ድንግል እመቤቱ ሆይ ከአበባ ምድር
የመፍለስሽ ምልክት፣
የሐዋርያትን ጉባኤ በሰማይ በደመና ላይ አሳየ፣
ውኪታውን በሰማን ጊዜ ለእኛ፣
የትንሣኤ ቀን የደረሰ መሰለን እስክሚሉ፣
ሙተው በመቃብር ሆድ ያሉትን በነጋሪት ድምፅ አስነሣ።

85. የታዴዎስ የስንዴ እሸት

ቀኝ እጁ በተከለሽ ቀን ፍሬ ያስገኘሽ የበርተሎሜዎስ ወይን፣
የታዴዎስም የስንዴ እሸት፣ አንቺ ነሽ፣
የቋውስጦስ መጠምጠሚያ፣ የጴጥሮስም ጥላ፣ ማርያም ሆይ!፣
በእንቺ ሙታን ሕያዋን ሆኑ፣
ሐዋርያትም በሰማይ መላእክትን ገዙ።

86. ማርያም ሆይ! ልጅሽ ምግብ ሆነኝ

ማርያም ሆይ! ልጅሽ ምግብ ሆነኝ፣
ከትሳዜዮም መረጋጊያ ተአምርሽን ለጠኝ፣
ቶማስም ጉኑን በዳሰሰ ጊዜ፣
በቁስሉ በጐ መዓዛ አገኙቱ፣
ከእጇ መልካም ሽቱ ፈሰሰ በማለት ተናገረ።

87. የጠራ ወርቅ ከበብ ነሽ

እመቤቴ! የሞቱ መታሰቢያ፣ የሰሙ ምልክት የተጻፈብሽ፤
ከሚያበራ የባሕርይ እንቁ የጠራሽ የራስ ወርቅ ከበብ ነሽ፤
የአበባ ጉንጉን የተሣለብሽ የጊዮርጊስ የመንግሥቱ ዘውድ
ማርያም ሆይ!፤
እንቺ ሁሉን ታሰግጂለታለሽ፤
እሱ ግን ለአንቺ ይሰግዳል።

88. የእስጢፋኖስ አበባ ነሽ

የፈውስ ምልክት ያለው የደመል ድምፅ ምሳሌ ማርያም ሆይ!፤
ከአበቦች ሁሉ የምትበልጭ የእስጢፋኖስ አበባ ነሽ፤
ከእሱ ጋር ያሉ ሰማዕታት የፈቅጦርና የአቦሊ ማኅበርም፤
የክርስቶስ እናቱ ሆይ የፍቅርሽን ድምፅ ሰምተው፤
ገዳዩን መከራ አላስታወሱትም።

89. ማርያም ሆይ! የፍቅርሽ ተአምር

ማርያም ሆይ! የፍቅርሽ ተአምር መራራውን አጣፍጦ፤
የሞትንም ጣር አስረስቶ፣ ድንቅ ነገር ይሰራል፤
በልጅሽ የፍቅር መዓዛ ለሰከረ ሰው ደግሞ፤
በድንጊያ መወገር ገለባ፤
በእሳትም መቃጠል ቀዝቃዛ ባሕር ይመስለዋል።

90. ማርያም ሆይ! አኑሪኝ

ማርያም ሆይ! እንደ ቀለበት በልብሽ ውስጥ አኑሪኝ፤
እንደ ማተብም ከፍ ባለች ክንድሽ አሰሪኝ፤
ለማዕታትን በሕይወት አበባ ከፍ ላደረጋቸው፤
ለፍቅርሽ ንብረቴን ሁሉ ሰጥቻለሁና፤
ንግሥት ሆይ! በበደሌ ሁሉ እንዳትንቂኝ።

91. ማርያም ሆይ! የፍቅርሽ ተአምር በጻድቃን ማኅበር

ማርያም ሆይ! የፍቅርሽ ተአምር በጻድቃን ማኅበር ተመሰገነ፤
ይልቁንም በኃጥኣን ላይ በእጅጉ ነገሠ፤
ሕመማንን ፈውሷልና፣ ሙታንንም አስነሥቷልና፤
የደረቀውንም አለመለመ የሚል አለ፤
ተራራውንም አፈለሰ የሚል አለ።

92. ሃይማኖቴ ማርያም ሆይ!

አጴጥሮስ ተዋጀሁሽ ሃይማኖቴማርያም ሆይ፤
ተራራን አፍልሰሽ በኢያሪኮ ዳር መሠረትሽ፤
የበደሌ ዘለፋ አንገቴ ባስደፋኝ ጊዜ፤
የአበባ ሙሽራ እናቴ የተአምርሽ መጽሐፍ፤
ኑዛዜና ተስፋን ያበሥረኝ ዘንድ እማፀንሻለሁ።

93. ማርያም ሆይ! የፍቅርሽ ተአምር

የተአምርሽ ፍቅር እሳቱን አጥፍቶ የባሕሩን ማዕበል አያረጋጋ
ዓለምን ዞረ፤
የክህነት ሽመትን ከመፍራት የተነሣ፤
መንቀጥቀጥን ተሞልተው፤
ሁለቱ ካህናት በማልጥ ከቆረጡ በኋላ፤
ከአንቺ እጅና አንደበት አገኙ።

94. የሐና አበባ ሆይ! ተአምርሽ

የሐና አበባ ማርያም ሆይ! ተአምርሽ በከሊፋ ፊት በታወቀ ጊዜ፤
በልጅሽ ትእዛዘ ወደ ሩቅ አገር ያደርስ ዘንድ፤
የመልእክት መጽሐፍ ይዞ ወጥ በረረ፤
ዓሣ አንበሪም ወርቅ ተሸክሞ፤
ጥልቁን ቀዝፎ ወደ ደሴት ወጣ።

95. ማርያም ሆይ የልጅሽ ተአምር ማድረግ

ማርያም ሆይ! ልጅሽ ተአምር ማድረግ በጀመረ ጊዜ፤
በትእዛዝሽ የጋኖቹን ውኃ ወደ ወይንነት የለወጠ
አይደለምን?
ኃይልሽ ምን መሥራት ይሳነዋል?
ሥልጣንሽን ለማሳየት ብትፈቅድስ፤
ድንጊያ እንኳን እንጀራ በሆነ ነበር።

96. በምስጋናሽ ውኃውን ቢባርከው

የሃይማኖት አበባ የተባለ የዋልድባመነኩሴ አባ ሳሙኤል፤
በቅዳሴሽ ጸልዮ ውኃውን ቢባርከው ጎበሰት ሆነለት፤
ማርያም ሆይ! ሁሉንም ማድረግ ትችያለሽና፤
ምሕረትና ፍትሕን ለተአምርሽ እቀኝ ዘንድ፤
ኃጢአቱን አስተስርዩ ጭንቀቱንም አቅልዩ።

97. ማርያም ሆይ! ቅዳሴሽ

ማርያም ሆይ! ቅዳሴሽ መለኮትን አበበ፤
ለቅዱሳንም ብቃትን አፈራ፤
ደቀ መዛሙርቱም የታሰሩትን ይፈቱ ዘንድ፤
በተመሰገነበት ቦታ ሁሉ ድንቅና ተአምርን አድርጉ፤
ለመምህራን ታላላቅ ኃይላትን አሳያቸው፤
ውኃውንም ወደ ጎበሰት ለወጠው።

98. አንድ ደሀ

ሃይማኖቱን የካደ አንድ ደሀ፤
ባሳተው በሰይጣን ፊት አንቺን መካድ እንቢ ባለጊዜ፤
ድንግል ሆይ! አንቺን ማመን ነፍሱን ለማዳን ጠቀመችውና፤
የልጅሽን ቸርነት ተአምርሽንም እያመሰገነ፤
ከአንቅልፉ ተነሥቶ ወደ ቤቱ ገባ።

ሮዘ ❀❀❀

99. ብዙ ለመደደችው ሴት

በብዙ ወዳው ሸቱ ለቀባችው ሴት፤
ልጅሽ ፈርዶ ኃጢአቷን ይቅር እንዳላት፤
ማርያም ሆይ! ብዙ ኃጢአቱን ይቅር በይኝ፤
የተአምርሽ ጠላት ግን ንስሓ ቢገባም እንኳ፤
ከኃጢአቱ መንጻትን አያገኝም።

100. የዮሴፍ ልጅ ዮሣ

ያስደነገጠሽን ወሬ ድንገት ከማምጣቱ በስተቀር፤
የዮሴፍ ልጅ ዮሣ ምን ኃጢአት ሠራ፤
ጻድቁ (እውነተኛው) በልጅሽ ትእዛዝ የሞተ አይደለምን?
ድንግል ለምን ዝም ትያለሽ ትዕግሥትንስ ለምን ታበዢያለሽ?
የተአምርሽን ጠላት ለማቃጠል እሳት አዝንሚ።

101. ተአምርሽን የሚያቃልለውን

መርገምን ሳይፈራ ተአምርሽን የሚያቃልለውን፤
ሰይጣን ተቀናቃኝ ልጹ አድርጐ በራሱ ተካው፤
ድንግል! ኃጢአትን አብዶ ዳግመኛ ሞትን እንዳያፈራ፤
ጠላትሽን ከቅርንጫፉ ጋር እንደ ዛፍ የሚቆርጥ፤
የሚያስፈራ የሞት ገጀሞን (ገጀራ) በላዩ ላኪ።

ክፍል ሦስት

102. ደካሞችን የምትረዳ ሆይ!

የሚረዳሽ የማትፈልጊ ድካሞችን የምትረጂ ሆይ!
ከአገልጋይሽ ወንበር ላይ ትዕቢተኛ ወራሹን በአንድ ጊዜ እንደገለበጥሽ፣
ድንግል ሆይ! ጠላቱን ገልብጠሽ ለመጣል ኃይልሽን ልበሽ፤
ተአምርሽን ሐሰት ብሎ የሚሳለቅ፤
ሰይጣን ይድን ዘንድ ይባዋልን?

103. ተአምርሽን የናቀ ሰነፍ ነው

አስቀድመሽ አንቺ ንቀሽዋልና የደመና አበባም /ደስታ/ አልፎታልና፤
ማርያም ሆይ! ተአምርሽን የናቀ ሰነፍ ነው፤
የደቅስዮስን አጽፍ /መጐናጸፊያ/ አስቦ፤
ዋጋ መቀበልን ከአንቺ ተስፋ በማድረግ፤
ተአምርሽን የሚጽፍ ግን ብልህ ነው::

104. ደቅስዮስ በጻፈ ጊዜ

ደቅስዮስ ቅዱስ ተአምርሽን በጻፈ ጊዜ፤
የድካሙን ዋጋ ወንበርና መጐናጸፊያ ወረሰ፤
ችግረኛውን የምታበለጽጊ ማርያም ሆይ!
የምስጋናየን (ማኅሌቴን) ዋጋ ልቤ ያሻውን ያህል፤
አበባ ያለው ልብስና አትሮንስን (ባለድጋፍ ወንበር) ስጭኝ::

105. ተአምርሽን የሚንቅ ኃጢአተኛ ነው

ጌትነቱን እንዳያይ ልጅሽ ከክብር አሰወግዶታልና፤
ማርያም ሆይ! ተአምርሽን የሚንቅ ኃጢአተኛ ነው፤
ነገር ግን የተአምርሽን ረድኤት እየነገረ፤
ሚስቱን ትቶ የሔደ አለ፤
መንግሥቱንም ንቆ ወደገዳም የገባ አለ።

106. የጽጌ መጽሐፍ ተአምርሽ

እንደተወዳጁ ልጅሽ ቅዱስ ወንጌል፤
የጽጌ መጽሐፍ ተአምርሽ በእኔ ዘንድ ክቡር ነው፤
ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፉብሽ የኪዳን ጽላት ማርያም ሆይ፤
ከቃልሽ አንድ ነገር ከሚወድቅ፤
የሰማይና የምድር ማለፍ ይሻላል።

107. የባሕርይ መጻሐፍ ተአምርሽ

ከአንደበቱ ሥር እንደ እሬት የእባብ መርዝ የሚተፉ፤
የአይሁድና የአረሚ መምህር አንደበትን አስቀድሞ የዘጋ
የባሕርይ መጽሐፍ ተአምርሽ፤
ከአባ ብንያሚ ልብስ በጐ ሽታ ይልቅ የአበባሽ መዓዛ ልብን
ይመስጣል፤
ማርያም ሆይ እንደ ላሚ መርገምን ተመልቶ ከፋኝ የሚናገር
የጠላትሽን፤
አንደበቱን በተአምርሽ ዝጊ።

108. የሕይወት መጽሐፍ ተአምርሽ

ተአምርሽ ከሞትና ከሲያል መሸጋገሪያ የሕይወት መጽሐፍ ነው፤

ገሃነም ከተባለ ዳግም ሞት በልጅሽ ሥልጣን ታድኚ ዘንድ፤

የዓለም ሁሉ ሕይወት እመቤቱ ሆይ፤

በከበቡሽ ልቅሶና አስጣሚ እንባ፤

በመከራዬ ጊዜ የማጎፀንሽን ፍሬ ልጅሽን ተማፀንኩ።

109. ተአምርሽ ሞላ

ተአምርሽ ሁሉን ቦታ ሞላ፤

ተራሮችንም በአበቦች ውበት ሸፈነ፤

ጎዘንን የምትሸሪ ደስታን የተመላሽ ማርያም ሆይ፤

ከገዳም እናት (እመምኔት) ማጎፀን ሕፃንን እንዳወጣሽ፤

ነፍሴን ከጎጢአት ሞት ፈጥነሽ አውጭ።

110. የእኔ ደም ምን ግዳጅ ይፈጽማል?

ወደ መቃብር ብወርድ የእኔ ደም ምን ግዳጅ ይፈጽማል?

የተአምርሽን ዜና መሬት ይናገራልን፤

የፍቅርሽ መዓዛ ሕሊናን የሚመስጥ፤

የቅድስት ሐና አበባ ማርያም ሆይ፤

የሕይወትና የጤና እድሜን ጨምሪልኝ።

111. በመታበር ማን ያመሰግነዋል

ጥበበኛው ሲራክ እንደተናገረ፤
ልዑል እግዚአብሔርን ማን በመታበር ያመሰግነዋል፤
በፍቅርሽ የተሳለ ጦር ተወግቻለሁና፤
ተአምርሽን በማጎሌተ ጽጌ አመሰግን ዘንድ፤
ድንግል ሆይ ረድም እድሜ አድይኝ።

112. ማርያም ሆይ! ደስ የሚያሰኝሽ

ማርያም ሆይ! ደስ የሚያሰኝሽን የጽድቅ ፍሬ አንድ ጊዜ አፈራ ዘንድ፤
ፈቃድሽንም እያደረግሁ በሕይወት እኖር ዘንድ፤
ማጭድ የሚሸከሙ (የሚሰነዝሩ) ክፉዎች የሞት መላእክትን፤
ከምስጋናየ ፍሬ ጥቂት ይገኝበት እንደሆነ፤
ይህን የተአምሬን ወይን አትቁረጡ በያቸው።

113. በወይን ቦታ ውስጥ

በወይን ቦታ ውስጥ አበባ ለፍሬ እንደሚያብብ፤
ድንግል ሆይ! የፍቅርሽ ተአምር በላየ ያብብ፤
ሰው እንኳን በሚዝግ ወርቁ የተዋጀውን ገንዘቡን አይንቅምና፤
ቃል በተባለ በልጅሽ ደም የተዋጀሁ እኔን፤
ኃጢአተኛውን አትናቂኝ።

ሸህ ❀❀❀

114. ለምን አሳዘንሞለሁ

ልጅሽ በደሙ የዋጀኝ ገንዘቡ እኔ፤
በከንቱ ጠፍቼ ለምን አሳዝንሞለሁ?
ምሕረትን የሚወድ አምላክ እናቱ ድንግል ሆይ ይትር በይኝ፤
ምሕረትም የልጅሽ ሕግ ነው፤
በዚህም ምስክሬ ተአምርሽ ነው፤

115. ማርያም ሆይ! አትዘንብኝ

ሞትሽንሽ ፍሬ ልጅሽ በመስቀል ላይ ያለበደል ቡጥቅሉው መከራ፤
ያዘንሽው የቀድሞ ኀዘን ይበቃልና ማርያም ሆይ! አትዘንብኝ፤
የልጅሽ ደም በደሜ ተጨምሯልና፤
በየቀኑ እየበደልኩ እኔ ባሳዝንሽም እንኳን፤
በምሕረትና በይቅርታ ተአምር አድርጊልኝ አንጂ አትዘንብኝ።

116. ክፉ የሞት ጣር

ክፉውን የሞት ጣር ማሰብ ልቤን ያስደነግጠዋል፤
ነገር ግን ተስፋ የሆነኝ ተአምርሽ እንደሚናገረው፤
ድንግል ሆይ! በእረፍቴ ቀን መጥተሽ፤
የገነት ዛፍ አበባን በላዬ ጣዪ፤
በመዓዛውም ነፍሴ ትመሰጣለች።

117. የቆላ ሱፍ አበባ

የደጋ ያይደለ የቄላ ሱፍ አበባን፤
በእሾሆች በአይሁድ መካከል ያስገኘሺ፤
ርኅራኄ ልማድሽ የሆነ የማዳን ተአምር ያለሽ ማርያም ሆይ!፤
መታመኔ በከንቱ እንዳይሆን፤
አማኝሽን እኔን ከጽኑ የሞት ጣር አድኚኝ።

118. ማርያም ሆይ ንገሪው

ማርያም ሆይ! በፀሐይ ሐሩር የደከመ ልጅሽን፤
ልጄ ሆይ በምድረ በዳ በስደት ጉዞ መድከሜን አስበህ፤
ለወዳጄ ከሲያል ሞት መዳንን አድለው፤
ለሕይወት /መዳን/ የተገባ ካልሆነ፤
እንባየ በከንቱ ፈሷልን በዪው።

119. በተአምርሽ አድኚኝ

ድንግል ሆይ! የአንቺ ልቅሶ በእጅጉ ስለሚበቃኝ፤
ዳግመኛ እንዳላለቅስ በተአምርሽ አድኚኝ፤
አንቺ የአዳምና የልጆቹ መድኃኒት ነሽና፤
ኃጢአተኞችን በጽድቁ እስከሚያድን ድረስ፤
ንጉሥ ልጅሽ እራቁቱን እንደተሰቀለ አስቢ።

120. ስለ አውሎጊስ ለዳንኤል

ስለ አውሎጊስ ለዳንኤል ስቅላትን በፈረደበት ጊዜ፤
ስለ ለው ፍቅር የሞተ የይቅርታ ተአምር ያለው ልጅሽን፤
እግሩን ስመሽ እንደማለድሽው፤
ድንግል ሆይ! እኔን ኃጢአተኛውን ይምረኝ ዘንድ
እያላለብሽው
አብዝተሽ አማልጂ።

121. ማርያም ሆይ ልጅሽ ይባረክ

ፍቅርሽ ልቤን የከፈለው የቃል ኪዳንሽንም፤
ይቅርታ ከእኔ ያልራቀ ማርያም ሆይ! ልጅሽ ይባረክ፤
የቃል ኪዳንሽም ምልክት ለዘማውያን ድንግልናን
ይሰጣል፤
የቃል ኪዳንሽ የመዳን ምክንያት ባይኖር፤
የእሳትና የፍዳ ወንዝ ሁሉን ባሰጠመ ነበር።

122. ልምላሜ እንዳለው አበባ ምንኛ መልካም ነው

ልምላሜ እንዳለው የርጥብ አበባ መዓዛ፤
ድሆችን በየጊዜው መጐብኘት ምንኛ መልካም ነው፤
ድንግል ሆይ! ስለ ቃል ኪዳንሽ ለበደለኛ በላኤ ሰብዕ፤
ከኃጢአቱ ይልቅ የውኃው ሚዛን ክብደት በበለጠለት ጊዜ፤
ለተአምርሽ በሰማይ ምስጋና ተደረገ።

123. ለልጅሽ ምን ዋጋ አከፍላለሁ

ድንግል ሆይ! ስለሰጠኝ የመዳን ምክንያት ስለ ቃል ኪዳንሽ፤
ለልጅሽ ምን ዋጋ እከፍለዋለሁ?
ነገር ግን ማርያም ከአንቺ ጋራ የተቻለኝን ያህል ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ፤
ልጅሽ ስለ አንቺ ያደረገልኝን ተአምር አስቦ የማይፈጽም፤
ለይጣን ግን አይቶ ያለቅሳል።

124. እስራኤል በልብሱ ጫፍ

እስራኤል ምልክት ይሆነው ዘንድ በልብሱ ጫፍ፤
ቢጫ ጎብረ መልክ ያለው ከአበባሽ ፈትል የዘርፍ ምልክት እንዳደረገ፤
ማርያም ሆይ! የመዳን ምልክት አድርጊልኝ፤
ክፉ የሞትን መልአክ ዐይን የሚበዘብዝ፤
ሰርድኖ የተባለ የእንቊሽን ብርሃንም በግንባሬ አመሳቅይ
(መስቀለኛ ቅቢ።)

125. የተባረኩ እርግቦች

በጥላሽ ሥር የሚያርፉ ፍሬሽንም ተመግበው፤
በደመ ቤኪይት የሚኖሩ እርግቦች (ምእመናን) በጒጎን ናቸው፤
የመስቀል ምልክት አምሳል ያላት የሽቱ ዛፍ ማርያም ሆይ!
አበባው አበባሽ ፍሬውም ፍሬሽ ነውና፤
ለሁለታችሁም (ላንቺና ለልጅሽ) ስግደት ይገባል።

126. ይህ መስቀል የመሰኮት ዘፋን ነው

ድንግል ሆይ! የኪሩብል አምላክ የሆነ የመሰኮት ዘፋን ይህ መስቀል፤
የፊደልና የገጽ አራትነት እንዳለው ሰምሽ፤
ከጠላት ፍላጻ በምናመልጥበት ምልክት ለተሰጠን ለእኛ፤
በኢየሩሳሌምና በግብጽ ውኃና ደም አፈሰሰ፤
እሱም ከድጥ የሚደግፈን መጠጣችንም የሆነ፤
የወይን ፍሬ የሚያስደሰኝ የመሰኮት ወይን ነው (ደመ መሰኮት)።

127. የልደት እና የጥምቀት ምልክት

ከልሙጥ ዐለትና ከደረቅ አጥንት በምድረ በዳ ለሕዝቡ
ውኃ እንዳፈለቀ፤
በጥምሽ ጊዜ ውኃ ያፈለቀ ግሩም የሆነ የልጅሽ ኃይል
አንቺ ጋር አለና፤
ማርያም ሆይ! በቀለም ከተሣለች ሥዕልሽ፤
ጡቶች ዘይትና ሜሮን በማፍለቅ፤
የልደትና የጥምቀት ተአምር አሳየሽ።

128. የኀዘን ክረምት ከላየ አለፈ

እነሆ! የኀዘን ክረምት ከላየ አለፈ፤
የምስጋናሽ አበባ ደስታም በልቤ ውስጥ ሞላ፤
ድንግል ሆይ! ከሥዕልሽ ወዝ እንደምታፈሺ፤
በጴጴንያ በተአምርሽ ተጽፎ እንደሰማሁ፤
በኢትዮጵያም ተትረፍርፎ አየሁ።

ሸህ ❀❀❀

129. ሥዕልሽ ሰው መሆንን አሰገንት

የገነት ዛፍ ለጌጥ እንደምታብብ፣
ማርያም ሆይ! ሥዕልሽ ሰው መሆንን አበበች፣
እመቤቴ የተአምርሽን ይቅርታ ለልጅ ልጅ አንገር ዘንድ፣
እውሬ በመርዙ አቁስሎኛልና፣
የሥዕልሽን ቅባት ቅቢኝ ከደዌም ፈውሽኝ።

130. የምትገኝበት ጊዜ አለ

ማርያም ሆይ! የሚያምር የአበባ ምልክት ያላት ሥዕልሽ፣
ከጥዑም የንግግር ቃል ጋራ የምትገኝበት ጊዜ አለ፣
ሥጋ ለብሳ የምትገለጽበት ጊዜም አለ፣
ርጉም አይዳዊ ሰው በሰይፍ በቆረጣት ጊዜም፣
ከእሷ ደም ተንጠፈጠፈ።

131. ሰውየ በተፋበት ቦታ

አንድ ከሀዲ ሰው የልጅሽን ቁርባን በተፋበት ቦታ፣
ሥዕልሽ ሕፃን ልጅ ታቅፋ በግልጥ ታየች፣
ዳግመኛም ከደሙ ጋር የቁርባን ጎብስት ሆነች፣
ይህን ድንቅ ሥራሽንም ያዩና የሰሙ፣
ማርያም ሆይ ለተአምርሽ ምስጋና አቀረቡ።

132. የልጅሽ ተአምር አበባ

የልጅሽ ተአምር አበባ ዐይኔን ያስደስታታል፤
ከእሱም ይልቅ ግርማን የተላበሰች የሥዕልሽ ወዝ በእጅጉ ያስደስታታል፤
የትንቢት ተክል ቦታ የአበባና የፍሬ ዘመን ማርያም ሆይ!
እስራኤል በጥዑም ዜማ ያመሰግኑሽ ዘንድ፤
ከበለስና ከወይናቸው ስር ከድካም አረፉ።

133. የዕጣን ቂጠሮ

አበባ ባለው የበዓል ልብስ አጊጣ፤
የአበባ ምንጣፍ እያነጠፈች፣ የቀጋ አበባም እየነሰነሰች፤
የልጅ ወንድሜ የዕጣን ቂጠሮ የእኔ ነው ብላ፤
በጐ ተአምርሽን ባመሰገነችበት ቦታ፤
ማርያም ሆይ! ነፍሴ ለሥዕልሽ ክብር ትሰግዳለች።

134. ሕፃን እንደሚደሰት

የመልክሽ ደምግባት የቀትር ፀሐይን እስኪሚ ያጨልም ድረስ፤
ለእኔ መዳን ደሙን ያፈሰ ዘንድ፤
የደስታ አበባ ያለው ፍቅርሽ፣ ልጅሽን አሳምሞታልና (በመሰቀል እስከ መስቀል አድርሶታል)፤
ሕፃን እናቱን ሲያይ እንደሚደሰት፤
እኔም ሥዕልሽን በማየትና በመሳለም እደሰታለሁ።

135. ያልነጣ አፈ ማኅፀን በሳጠ ጊዜ

ጠላትን አሳፍሮ የፍቅርሽን ተአምር ይገልጥ ዘንድ፤
ከመንጻት ጊዜ ሰዓተኛ ቀን በፊት ያልነጻ አፈ ማኅፀን በሦመ ጊዜ፤
ማርያም ሆይ! ሥዕልሽ የትንሣኤ አበባ ዮሐንስን፤
ሁለት ጊዜ አፈወርቅ አፈወርቅ ብላ፤
በጉባኤው ሁሉ ፊት አመሰገነችው አወደሰችውም።

136. ማርያም ርኅራኄሽ

የልጅሽን ትእዛዝ በማጉደል በአንቺ ግን የተማፀነ መልአክን ርኅራኄሽ ሕፃናትን እንዳይቀስፍ አስተወው፤
በሰነው ፈጣሪ ፊት ተመልሶ ለመቆም ማረግ ኩተሳነውም ቦኂላ፤
ወደ ቀልሞን ተራራ ወጥቶ ሳሙኤል በጸለየበት ጊዜ፤
የሥዕልሽ ተአምራዊ ኃይል ወደ ሰማይ ነጠቀው (ዐሳረገው)፤

137. የተሞበች ሥዕልሽ

በወዝ የተዋበች ሥዕልሽ በዓለም እንደዚህ ካማረች፤
ማርያም ሆይ! የፊትሽ ደም ግባትማ በሰማይ እንደምን ያምር፤
ዝናብ ያጠፋው ዘንድ የማይችል፤
የፍቅርሽ እሳት ፍሕም አቃጥሎኛልና፤
የተአምርሽን ደስታ አይቼ እጠግብ ዘንድ በሕልም ተገለጭልኝ።

138. በደብረ ምጥማቅ በተገለጥሽ ጊዜ

የፊትሽን ምልክት ያይ ዘንድ የሞተ እሰኪነሣ፤
በደብረ ምጥማቅ አምስት ቀን በተገለጥሽ ጊዜ፤
ማርያም ሆይ! ምን ያህል ታስደስቻለሽ?
የፍቅርሽን አበባ በቀን በንቃት ማየትን ተይውና፤
ሌሊት በሕልሙ ያየሽ ብፁዕ (ንዑድ-ክብር) ነው።

139. እንስራዎችን ይጭን ዘንድ

በአንበሳ ጀርባ እንሰራዎችን፤
በጠላት በሰይጣን ራስም ድጊያን፣ ይጭን ዘንድ፤
ልጅሽ ለሰርያ ሰው ለአሮን ሥልጣን ሰጠው፤
ታምርሽ የበዛ የደብረ ምጥምቅ አበባ ማርያም ሆይ!
ለክብርሽ የሚገዛ ሁሉን ያስገዛል፤
አጋንንትንም እንደባርያ ይገዛል።

140. ማርያም ሆይ በፍቅርሽ የተከል ቦታ

ማርያም ሆይ! ብዙ የምስጋናሽ ፍሬ እጥፍ ድርብ እስኪሆን፤
በፍቅርሽ የተከል ቦታ የምልክት እሸት ተገኘ፤
ልብ የሚሰልብ ሽታው የየራሱ የሆነ አበባ፤
ጣዕሙም የየራሱ የሆነ ፍሬ አስገኙት፤
ልሳነ እፍረት የተባለ ጊዮርጊስም በጐ መዓዛን ሰጠ።

ያሬ ♦♦♦

141. በሦስት ድንጋዮች የአካል ሦስትነቱን ለማሳወቅ

ድንግል ሆይ! በሦስት ድንጋዮች በገጽ ሦስትነቱን ለማሳወቅ፤
የቤትሽን ሕንፃ መሠረት ከፈጸመ በኋላ፤
ከአንቺ ጋር በአንድነት ለበዓል በወረደ ጊዜ፤
ልዑል አምላክ ማደሪያውን መረጠ እያሉ፤
ቃል አውጥተው ለመዘመር፤
ደናግል ለልጅሽ ከበሮውን መቱ።

142. ዑራኤል ለሄኖክ

ዑራኤል ለሄኖክ ያሳየው መልኳ በረዶ፣ ጠፈርዋም መብረቅ፤
የሆነች የእሳት ቤት የምሳሌሽ ምልክት ናት፤
የነጐድጓድ አበባ ድንግል ሆይ! አስቀድመሽ እንደተናገረሽ፤
ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉሻል፤
ከእነሱም አንዱ እኔ አገልጋይሽ ነኝ።

143. ወደ ተራራዎች ብወጣ

ወደ ተራራ ብወጣ ወደምድረ በዳም ብወርድ፤
በፍጹም አንቺን የሚመስል አበባ አላገኘሁም፤
አስደናቂ ተአምርሽን ደጋግሜ አመሰግን ዘንድ፤
ድንግል ሆይ! የሚጥም የሕፃናትን ምስጋና አስሚኝ፤
በቀኝሽ መቆምንም አድይኝ።

ያዕ ❀❀❀

144. ውበትሽ ያንጸባርቃል

ከመልካም ሽቱ ይልቅ የከበርሽ ፤
ብርኩማሽም የከበረ የሰማይ መ·ሽራ ማርያም ሆይ!
በታሕሣሥ ወር እውነተኛ ፀሐይ ጌታን ወልደሻልና፤
ከእንቊምችና ከአበቦች ውበት ይልቅ ውበትሽ ያንጸባርቃል፤
ከቁጥር የሚበዛ (ስፍር ቁጥር የሌለው) ተአምርሽን፤
በእርጅና ዘመኔ ሁሉ እስከምነግር ድረስ አትተይኝ።

145. ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ተአምር

ማርያም ሆይ! የወንዝ ዳር እንኩይ በማለት ያመሰግንሽ ዘንድ፤
የፍቅርሽ ተአምር የልቤን ሐሳብ አነሳሳው፤
እግዚአብሔር እንደባረከው እንደ ዱር አበባ ሽታ፤
በወይን ሐረግ መልክ ወርቅ የተዘመዘመበት የልብስሽን ሽቱ አሸት ዘንድ፤
ንግሥት ሆይ ከጥላሽ ሥር መጠጋትን ፍቀድልኝ።

146. እንደ ልብስሽ ሽታ

ከገነት አበቦች ከምድረ በዳ ዕፅዋትም፤
በውኑ እንደ ልብስሽ ሽታ፣ እንደ አፍንጫሽና አፍሽ መዓዛም የሚሸት አለን?
የኪሩብ የእጣኑ ጢስ የተአምር ቁርባን ማርያም ሆይ!
የተቋጠረ ዕጣን ነውን? ሽቱ ነውን?
የአንቺን መዓዛ የሚመስል የለም!!

147. የሰማይ ጌጥ

የዓመታት ምልክት የሰማይ ሽልማቶች፤
ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት፤
የምድር ሽልማቶች የአበቦች ውበትም፤
እንደ ጥላ በድንገት ያልፋሉ፤
ንግሥት ማርያም ሆይ! ያንቺ ፤
ምስጋና ሽልማትሽ ግን ለዘለዓለም አያልፍም።

148. ማርያም ሆይ ተአምርሽ ቢጻፍ

ማርያም ሆይ! ተአምርሽ በእያንዳንዱ ቢጻፍ፤
ዓለም እንኳን ሊሸከመው ባልቻለ ነበር፤
ለሕፃን በአበባ መጫወት ልማዱ ነውና፤
እንደ ልማዱ ይደሰትበት ዘንድ፤
የአንደበቴን አበባ በልጅሽ እጅ ላይ አስቀምጭ።

149. የደሴት ጽጌረዳ አይደለም

ጐንበስ ብየ ያቀረብኩልሽ የተአምር እጅ መንሻ፤
የባሕር ሽቱና የደሴት ጽጌረዳ አይደለም፤
መለወጥ የሌለብሽ ሰውን የመምትወጂ ማርያም ሆይ!
የአንደበቴን አበባ ጥቂቱን አብዝር፤
መልካም ሽታውንም በአፍንጫሽ ጨምሪ።

150. የተአምር ምስጋና አቀረብኩልሽ

ሃምላ ስለሚሆኑ የሥዕልሽ የራስ አክሊል አበቦች ልክ፤
በየሃምላ የሚሠለስ የተአምር ምስጋና አቀረብኩልሽ፤
ይህን ተቊበልሽ የሚያሳ አንበሳ መቃብሯን እስኪቆፍር ድረስ፤
ግብፃዊት ሴትን ከርኩሰቷ እንዳነፃሻት፤
እኔንም ከበደል (አንጭኝ) ንጹሕ አድርጊኝ።

151. ምንም አያስፈለገኝም አትበይ

ከእሴይ ወገን የተገኘሽ የመድኃኒት አበባ ማርያም ሆይ!
ከጻድቃን አንደበት የተገኘ፣ ያለኝ ምስጋና ይበቃኛልና፤
ከኃጢአተኛ አንደበት ምንም አያስፈልገኝም አትበይ፤
እኔን በደለኛውን ከተቀበልሽም፤
ተአምርሽን ጨረቃ ያመሰግናል።

152. የሐና አበባ ማን ነው

የሐና አበባ ሆይ! የውዳሴሽን የሽቱ አዝመራ የለቀመ ማን ነው?
ተአምርሽን እንጀራ፣ ምስጋናሽንም መዓር፣ አድርጎ፤
የተመገበና የጠገበስ ማን ነው?
እመቤቴ ንግግሬን በሰው ሁሉ አንደበት፤
ደዌን የሚፈውስ፣ ነውርንም የሚያነሣ ስኪር አድርጊልኝ።

153. ተአምርሽን በማሰብ

ተአምራትሽን በማሰብ አሳቦቼ ሁሉ ተሰቀሉ (ተመሰጡ)
በልቤ መካል ፍቅርሽ በቅሏልና፤
በከንፈሮቼም የምስጋናሽ ቅርንጫፍ ለምልሟልና፤
ማርያም ሆይ! ያዩት ሁሉ ፊደሉን ያነቡ ዘንድ፤
ምስጋናዬን በቅጠሉም በአበባውም ጻፉ።

154. ይህን ምስጋና ይህንንም ማጎሌት

ይህን ምስጋና ይህንንም ማጎሌት፤
ተአምርሽ አብቦ አፈራልኝ፤
ድንግል ሆይ! ዘንባባ ተሸክሜ ዳግመኛ አመሰግን ዘንድ፤
በበጉ ደም ልብሳቸውን ከአጠቡት ጋር በአንድነት፤
በብርሌ ባሕር መቆምን አድይኝ።

155. የአረንጓዴ ቀይና ቢጫ ዐይነት

ንጹሕ የተአምርሽ ቀስት (5 ቀስተ ደመና የማርያም መቀነት)
እንደ ብር ገንቦ ጌጥ፤
በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ዐይነት በወርቅ አምሳል የተሠራ ነው፤
የሰማይና የምድር ንግሥት ሆይ! የተወደደ የጽጌ ምስጋና
ተፈጽሟልና፤
ውድሽ ከጕንሽ እንደሚጠጋ /እንደሚቀርብ፤
የቀጣዩን ዓመት ምስጋና በሰላም አቅርቢልን።

156. ፕበበኛ አዋቂ ማን ነው?

ደቃቅ የባሕር አሸዋና የሰማይ ከከቦችን ቆጥሮ፤
በመረዳት ከሚያውቅ ልጅሽ በቀር ጥበበኛ አዋቂ ማን ነው፤
ማርያም ሆይ! ቅዱስ ኤፍሬም ለምስጋናሽ እንደተጋ?
ተአምርሽን ጠንቅቀን ተናግረን አንጨርስምና፤
ምስጋናሽን በጥቂቱ ተናግረን ዝም እንበል።

157. ለአብ ምስጋና ይገባል

ለአብ ምስጋና ይገባል ለወልድም ምስጋና ይገባል፤
መፈጸም ላስቻለኝ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና /ሰላምታ/ ይገባል፤
ማርያም ሆይ! ተአምርሽን ማንበብ በጀመርኩበት ጊዜ፤
በአማላጅነትሽ ለሕይወቴ መንገዱን አቅኝ፤
ለልቡናየም ምኞቱን ፈጽሚ፤

158. ምስጋና ይገባሻል

ማርያም ሆይ! ትጉኃን መላእክት ባቀረቡልሽ አበባ ምስጋና ይገባሻል፤
ማርያም ቅዱሳን ነቢያት ባቀረቡልሽ አበባ ምስጋና ይገባሻል፤
ማርያም ሆይ! ወንጌልን የሰበኩ ሐዋርያት ባቀረቡልሽ አበባ ምስጋና ይገባሻል፤
ማርያም ሆይ! ጻድቃንና ሰማዕታት ባቀረቡልሽ አበባ ምስጋና ይገባሻል፤
ዳግመኛም በልጅሽ ሥጋና ደም ያዘነ ይደሰታልና፤
በልጅሽ ሥጋና ደም ምስጋናም ምስጋና ይገባሻል።



ዋጋ፡- ብር 80.00

አጋሚ ማኅበረ ቅዱሳን ኅትመት አገልግሎት